# መሸጥ የለመደ እናቱን ያስማማል

ስለ ጉራጌ ጎሣ በፌስ ቡክ ላይ የተከትቡ አንዳንድ መጣጥፎችን ከተመለከትኩ በኋላ ስሜቴን ስለኮረኮረኝ እኔም የቺን ትንሽ ልበል አልኩ። የጉራጌ ጎሳ ለፍቶ የሚያድር ፤ታታሪ እና ጨዋ ሕዝብ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉንም ሥፍራ እንደ ትውልድ አካባቢው በመቁጠር በስራ ተሰማርቶ፤ ከነዋሪው ጋር ተግባብቶ ተከብሮና አክብሮ በፍቅር የሚኖር ሕዝብ ነው። የአገርን ሕልውና የሚፈታተን ጥያቄ ሲቀርብም ቅሌን ጨርቄን ሳይሉ ጥሪውን የሚቀበሉ የጀግኖችመፍለቂያ ነው። እንድ ምሳሌም ማቅረብ ካስፍለገ የመድፉን አባት ጀነራል ወልደስላሴ በረካን እንዲሁም የኢትዮጵያ ወደር የሌለው የጀግና ከፍተኛ ሜዳልያ ተሸላሚ ጀግናው ጀነራል ተሰፋዬ ሐብትማሪያምን ያፈራ የጉራጌ አፈር ነው። ይህንን ጀግና ጠላት ሣይቀር ወደር የማይወጣለት ጀግንነቱን በማድነቅ ጀግናው ሰብሮ የወጣውን አዳጋች ሥፍራ "ተስፋዬ በር" ብሎ በጀግናው ስም ሰይሞታል። በኢትዮጵያዊነታቸው የሚኮሩ ሕልውናችን፤ እስትንፋሳችንም ሆነ ሁለመናችን ኢትዮጵያ ከሚሉት ሚሊዮኖች መካከል የሚጠቀሱት ምሁር ዶክተር ያዕቆብ ሐይለማሪያም እነ አምባሣድር ታደሠ ገብረኪዳን ወዘተ የዚሁ ጎሣ ተወላጆች ናቸው።

እንግዲህ ወደ ቅርብ ጊዜው ታሪክ ስንገባ ደግሞ ግንቦት 97ን ተከትሎ የተፈጠረው ግንቦት 7 ሃሰት ተፈጥሮው ዕድገቱና ሕልውናው ሆኖ ውስጠ ባዶ አካሉ ግዙፍ ሳይሆን ገዝፎ ለመታየት እየሞከረ ያለ ድርጅትነው። ከተቀቀለ ባቄላ መካከል ጥሬ እንደማይጠፋ ሁሉ ከዚህ ድርጅት ዘጠኝ ዐመራር አባላት መካከል አምስቱ ጉራጌዎች በመሆናቸው የጉራጌን ህዝብ ስም እያስነሱ ይገኛሉ። በርግጥ የዚህ ድርጅት መስራች ብርሀኑ ነጋ በፖለቲካ አቋሙ የተረጋጋ ሕይወት ኖሮት እንደማያውቅ የነበረባቸው ድርጅቶችም ሆኑ በቡድን አበረው የሰሩ ሁሉ አበከረው የሚያውቁትና የሚናገሩት ሃቅ ነው።

ከኢህአፓ፡ ከአፍሪካ ቀንድ፡ከመለሰ ዜናዊ፤ ከነ ክፍሌ ወዳጆ፡ ከነ እንድሪያስ እሸቴ፤ከታምራት ላይኔ ከቀስት ደመና፤ ከቅንጅት ወዘተ ጋር ሁሉ አብሮ የሰራ ሲሆን በሁሉም ዘንድ ስለግለሰቡ የሚሰነዘሩ አስተያየቶች፤ሃሰት ምሱ ውሸት ልብሱ፤ ዕምነት ሊጣልበት የማይቻል፤በማናቸውም ሁኔታ የራሱን ጥቅምና ፍላጎቱ ያሟላል ብሎ የገመተው ጉዳይ ካለ ያለምንም ይሉኝታ የጀመረውን ጥሎ ወደአሰበው የሚጓዝ ሥልጣን ወዳድ አድርገው ያቀርቡታል። የህንኑ ሁኔታ በማስረጃ ለማረጋገጥም

- መለስ ዜናዊ ሥልጣን ከመያዙ በፊት በዋሽንግትን ዲሲ ከተማ ሬነሳንስ ሆቴል ተገኝቶ ኢትዮጵያን ለማፈራረስ ባወጣው ዕቅድ ላይ በተደረገው ውይይት ተሳታፊና ተባባሪ እንድነበር ፤

- ወያኔ አዲስ አበባን በያዘ ወቅት የአፍሪካ ቀንድ የሚባለው ስብስብ አባልነቱንና እምቢልታ የሚባለውንና በሐላፊነት የሚመራውን ስብስብ ደግሞ በአውላላ ሜዳ በትኖ ሹመት ፍለጋ መሄዱን፤

- አርባ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህራን ሲባረሩ በእነሱ ምትክ ደሞዝ ሳይከፈለኝ በነጻ አስተመራለሁ ብሎ በተግባር ለትግራይ ወያኔ ጸረ ምሁራን ውሳኔ ተባባሪነቱን፤

- በኢድፓ፤በሕብረት፤ በመድህንና በመኢዕድ መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት ዕርቅ አውራጅ መሰሎ ሁሉንም ወገን በመሰለል ቅሬታቸውን ወደ ተባባስ ቅራኔ አዳርሶ በመካከል ቀስተ ደመና የሚባል ድርጅት ማቋቋሙን፤ በመዘርዘር የገልጻሉ።

መቼም ያ የ1983 የነጻ አውጭዎች ግርግር በአዲስ አበባ ሲፈጠር በወቅቱ የአሜሪካ ነዋሪዎች ዜናውን ሳትሰሙ እንድልቀራችሁ እገመታለሁ። በዚያው ሰሞን አካባቢ የዚያን ጊዜው የእምቢልታ የዛሬው የግንቦት 7ቱ መሪ ብርሃኑ ነጋ ፤የእምቢልታ አባላቶችን በትና ተቋሙንም አፍረሶ ሥም ሊያውጣ ፤ሊሾም ሊሸለም ወደ አዲስ አበባ ነጎደ። በወቅቱ በጸረ ደርግ አቋም የሚታውቁ የሃይማኖት አባቶችም እነ አቡነ ጳውሎስ፤ አቡነ ማቴዎስ እንዲሁም ነፍሳቸውን ይማረውና የለንደኑም አባ አረጋዊ በኋላም አቡነ ዮሃንስ የተባሉትና ሌሎች ሆድ አደሮች ወደ አዲስ አበባ ለሹመት ከነጎዱት ከነብርሃኑ ነጋ ጋር የሚደመሩ ናቸው።

ያ ወቅት ጸረ ኢትዮጵያ የሆነ ብሄረተኛ ቡድን ሁሉ እዩኝ እዩኝ ያለበትና የዐንድነት ሃይል ደግሞ አንገቱን የደፋበት ጊዜ ነበር። የሚደሰኮረው ጽንፈኝነትን የተላበሰ የብሄረተኛነት ፕሮፖጋንዳ ሲሆን የደርግ መንግስት ደጋፊዎች ናቸው በሚል ብዙዎች በእስር ላይ የነበሩበት፤ ከሚታሰረው ሕዝብ ብዛት የተነሳም ማሰሪያ ስፍራ በመጥፋቱ ብዙ ቪላ ቤቶቸ እንደ እስር ቤት ያሚያገለግሉበት ጊዜ ነበር። ጊዜና ጥላ ሳይታሰብ ያልፋል እንዲሉ የትግራይ ነጻ አውጭ ድርጅት አዲስ አበባን ከተቆጣጠረና በወቅቱ የነበረውም የነጻ አውጭ ነን ባዮች ግርግር ዐመታትን እያስቆጠረ ቢሆንም፤ ያ ወቅት ለብዙዎቻችን በዐይነ ህሊናችን የትላንት ሲኦላዊ ትውስታን፤ በዕዝነ ልቦናችንም ጥሎት የሄደው ስብራት እስካሁንም አልጠገገም።

ከዐማራው በስተቀር በነጻ አውጭ ስም የተሰባሰቡ የዚያን ጊዜው ባለመድረኮች ሁሉ፡ከኢትዮጵያ ጋር ቅራኔ አለን ባዮች ነበሩ። ስለኢትዮጵያዊነትና ስለ አንድንት መናገር እንደ ከፍተኛ ወንጀል ይቆጠር ነበር። የሚገርመው በስርቆት ደረቅ ወንጀል ከሕግ አምልጦ የወጣ ሁሉ እንደ ባለወለታ፤ ታጋይና አርበኛ ተቆጥሮ ተሿሚና የአዲሱ ለውጥ አርማጅ በመሆን ሽር ጉድ፤ ጠብ እርግፍ የሚሉ ዘመነኞች ነበሩ።

እዚሁ ላይ አንድ ታሪክ ላንሳ፤ በደርግ ዘመን ማዕከላዊ ዕስር ቤት ታስረን ሳለ ብዙ የአነግ ቱባ ቱባ ባላስልጣኞችና የተወሰኑ ተከታዮቻቸው እስረኞች ነበሩ። በመከራ ቤት የተገናኘ መቼም የሆድ የሆዱን ባየጫወትም አልፎ አልፎ ያሰረውን ክፍል መውቀስና መኮነን፤ በአገር ፖለቲካ ጉዳይ ላይ ሀሜት አዘል ውይይት ማድረግ የተለመደ ነበር። በውይይቱ መግባባት አለመግባባት ቢኖርም ያለነው በሕግ ጥላ ሥር ስለሆነ የመጨረሻው መዳረሻው አለመወያየት ወይም መኳረፍ ሊሆን ይችላል። በተለይም በዚያን ወቅት እስረኛ የነበረው ሁሉ የሚያስታውሰው በእስረኛው መካከል የሚናፈሱትን ወሬዎች ልዩ ልዩ ስም ይሰጣቸው ነበር። ለምሳሌ ሞገድ (ሞራል ገንቢ ድርጅት)ተአድ(ተስፋ አስቆራጭ ድርጅት)ውነድ (ውዥንብር ነፊ ድርጅት) ወዘተ እንዲሁም እገሌ ሠላይ ነው እስረኛውን ሊሰልል የመጣ ነው የሚሉና ተመሳሳየነት ያላቸው አግላይ የአሉባልታ ዘመቻዎች ይካሄድ ነበር። ስለዚሁ ጉዳይ ምናልባት አንድ ቀን ጋሼ አሠፋ ጨቦ በሰፋት በተባው ብዕራቸው ያስነብቡን ይሆናል።

ወደ ገደለው ልግባና፤ የአነግን አቋም በተለይም የፖለቲካ አፍ መፍቻ ጥያቄያቸው 'የአበሲኒያ የቅኝ ግዛት ጥያቄ' እንደሆነ የሚያቀርቡት ትክክል እንዳልሆነ ከማሳየትም በላይ ይቃወሙት የነበሩ ብዙዎች ነበሩ። በ1983 ዓ.ም ቅኝ ገዥው ወያኔ ህወአት በአዲስ አበባ ሥልጣን ሲይዝ በሌንጮ ለታ የሚመራው አነግ አንዱና ከፈተኛው የሥልጣን ተካፋይ ነበር። ታዲያ! የሚገረመው አነጎች በመከራው ዘመን በዘብጥያ ሆነው በውይይት ያልተግባቡአቸውን ግለሰቦች ቂም በመያዝ ያሉበትን ስፍራ እያነፈነፉ ማሳደድና

ማሰቃየት የዕለት በዕለትሥራቸውና ተገባራዊ ድርጊታቸው ነበር። ለነገርዬው በዚህ ተግባር የተሳተፉት የኦነግ ጀሌዎች ብቻ ሳይሆኑ ዋና ዋናዎቹም መመሪያ በመስጥት እጃቸውን እንዳስገቡ ይታወቃል።

ኦነግ በዚያች ጥቂት የስልጣን ዘመኑ በልዩ ልዩ ሥፍራዎች በዘረኝነት ተነሳስቶ የጅምላ ጭፍጨፋ ፈጽሟል። በባሌ፤ በአርሲ፤ በአርባጉጉ፤ በሐረር በገለምሶ፤በቦርደዴ፤በመቻራ፤ በአሰቦት፤በሂርና፤ በአሶሳ፤ በጂማ፤ በቤኒሻንጉል ወዘተ የሰው ልጅ ይፈጽመዋል የማይባል ወንጀል ለመፈጸሙ 'ምጸዐት ዐማራ' የሚባለውን በሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ተዘጋጅቶ የቀረበውን መጽሃፍ ማንበቡ በቂ ነው።

የኦነግን የወንጀል ታሪክ ምጸዐተ ዐማራ ከበቂ በላይ መረጃን ያካተተ ሲሆን የዐለም አቀፍ የወንጀል ህግ ባለሙያዎች ለሰው ልጅ ህልውናና ደህንነት እንዲሁም ለሙያቸው ልዕልናና ክብር በእውነት ቆመናል ካሉ ለተጎዱ ወገኖቻቸው የህሊና እርካታ እነሌንጮ ለታ፤ዲማ ነገዎ ና ሌሎችም በወንጀሉ የተሳተፉ ጀሌዎቹን ለሕግ ሊያቀርቡ ይገባቸዋል።

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅትም ይሕን በታሪክ ለዝንተ ዘመን ህያው ሆኖ የሚኖር መጽሐፍ ከነሙሉ ማስረጃው አዘጋጅቶ ማቅረቡ የወገኑን አደራ መወጣቱን ቢያረጋግጥም፤ ወደፊት አንድ የተግባር እርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል። ይኋውም እነ ሌንጮ ለታ ከገንጣዩ ወያኔ ጋር በመሆን ከጀርመን ፋሽሽቶች ባልተናነሰ በወገናቻችን ላይ ለፈጸሙት ወንጀል ተጠያቂ ስልሆኑ፤ በመላው ዐለም ለሚገኙ ወገኖች በማሳወቅ በጉዳዩ ፈቃደኛ የሆኑ የህግ ባለሙያዎችን አሰባስቦ አንድ ጠንካራ ዐለም አቀፍ አስተባባሪ ኮሚቴ በማቋቋም የህግ የበላይነት የሚጎመራበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት።

እንደው ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ የተጠቀሰውን ጉዳይ እግረ መንገዴን አነሳሁት እንጂ የነገር ጭብጤ መነሻ አልነበረም። ግነቦት ሰባት ከጉራጌ ህዝብ ጋር የሚያያዝ አይደለም። በርግጥ አንዳንድ ብስለት አልባ ተወላጆች በጭፍን ድርጅቱን ሲደገፉ የታያል። ይህም የሚጠበቅ ነው። ዕውነቱ ግን ይህ ድርጅት የአንድን ግለሰብ የስልጣን ጥም ለማርካት የተቋቋመ ድርጀት ነው። ከስሙ እንኳን ስንነሳ ኢትዮጵያን አመልካች አንዳችም ቃል አልያዘም ። ይህም የሚያመለክትው ወያኔ የፈጠረውን የ83 ዓ.ም ግርግር ድጋሚ ለመፈጥር ዐላማቸው አድረገው የተነሱ የደቡብ የበላይነት የሚሉ የጥቂት ወሮበላዎች ሕልምና ዕኩይ ተግባር ለማከናውን የተፈጠረ ድርጅት ነው።በዚሁ ድርጅት ውስጥ ዕውነት ትግል ያለ መስሎት ገንዘቡን የሚከሰክስ ቀቢጸ ተስፈኛ ሆዳም ዐማራም ይገኝበታል። 500 ብር አምጡ ነጻነትን በስድስት ወር ጊዜ እንሰጣችኋልን ብሎ ገንዘብ የሰበሰበው ድርጅት እንኳን በሰድስት ወር በአስር ዐመት ያመጣው ልውጥ የለም።

ግንቦት 7 ከተቋቋመበት ጊዜ ጀመሮ በየጊዜው ከአምስት በላይ ልዩ ልዩ ስብስቦች ጋር ያደረጋችውን የጥምረት፤የህብረትና ግንባር የመፍጠር ሥምምነቶች ኢትዮጵያ የሚለው ሥም እንደ ኮሶ የሚጎፈንናቸው ፤የነጻ አውጭ ንቅናቄዎች ወይንም ገንጣይ ብድኖች ለመሆናቸው ያለፉበት ታሪክ ምስክር ነው። በመሰረቱ ይህ የጥምረት ጋጋታ አንድም ቁምነገር ስይታየበት የአንድ ስሞን ሆይ ሆይታና ገነዘብ መሰብሰቢያ ሆኖ ከማለፍ በስተቀር የፈየደው አንድም ነገር የለም። ይህ የአንድ ሰሞን ሽብ እረብ ግንቦት 7ን እንደ ትልቅ ድርጅት አግዝፎ በአንዳንዶች ዘንድ ለማሳየትና በዲያስፖራው መካከል ከፋፋይ ውዥንብር በመንዛት ለገንዘብ ስብሳቦሽ አግዞ ይሆናል። ነገር ግን ዘለቄታ የሌለው ጉዞና በድቡሽት ላይ የተሰራ ቤት ሳይታስብ እንደ ወዝቦ ንፋስ መጣ ሲባል የሚያልፍ ይሆናል።

በተለይም በወልቃይት ጠገዴ አካባቢ ጦርነት መጀመሩን አብሳሪ ፊሽካ ተነፊቷል ከመባሉ ከጥቂት ግዜያት በፊት  በክሊቭላንድ ኦሃዮ ወደ አስራ አስራ ዐራት የሚሆኑ የጎንደር ተወላጆች ከብርሃኑ ነጋ ጋር ስብሰባ አድረገው ነበር። እንዚህ ግለሰቦች የተሰባሰቡት ከኮለንበስ ኦሃዮ፤ከዴንቨር ኮለራዶ፤ ከአትላንታ ጆርጂያ፤ ከቶሮንቶ ካናዳ፤ ከሴንት ሉዊስ ሚዙሪ ወዘተ ሲሆን የሰበሰባቸውም ዋና ዐላማ በጎንደር ከፍለሃገር የሚንቅሳቀሱ በዱር በገደሉ የሚኖሩ ተራ ሽፍታዎችን በማሰባሰብ የግንቦት 7 ሰራዊት ጥንሥሥ ለማዘጋጀት እንዲቻል ለመመካከር ነበር። በቂ ገንዘብ ከተገኘ ይህ እቅድ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኋላ ይህንኑ ለማስፈጸም ከሰብሰባ ተካፋዮች ብቃትና ስፊ ግንኙነት አላቸው ለተባሉ ግለሰቦች ገንዘብ ታድሎ  የሽፍታ አደናው እንዲቀጠለ ስምምነት ላይ መደረሱን አፈትልኮ ከወጣ መረጃ ለማወቅ ተችሏል።

በዚሁ መሰረት የሙከራ እንቅስቃሴው ተገባራዊ ሆኖ የተውሰኑ ሽፍቶችን ለማደራጀት ተሞክሯል። ከተገኙት ሽፍቶች መካከል ደሳለኝ ዋርካው የተባለው ሽፍታ በወህኒ ቤት የሚገኙ የህግ እስረኞችን ለማስፈታት የተሰጠውን  ተልዕኮ ሳይውጣ በእስርኛ ጠባቂዎች ተገድሏል።ምንም እንኳን ኢሳት የነጻነት ታጋይ ተሰዋ ብሎ የግለሰቡን ገድል ቢተርክም፤  ግለሰቡ ተራ ወንበዴ ሽፍታ ነበር። ከረዥም ጊዜ  ስደት በኋላ ከአሜሪካ ቤተሰቦቻቸውን ጎንደር ለመጠየቅ በሄዱ ወገኖቻችን ላይ የፈጸመው ወንጀል እጅግ አሳዛኝ ነው። አቶ ደማሴ ገላጋይ የእንገዶቹ ወላጅ አባት ልጆቻቸውንና የልጅ ልጆቻቸውን ለመቀበል ወደ ባህርዳር የሄዳሉ። ልጆቻቸውን የልጅ ልጆቻቸውን ካገኙ በኋላ ይዘው ወደቤታቸው ጎንደር ሲጓጓዙ ይህ ወነበዴ ከዱር ወጥቶ ያስቆማቸዋል። የያዙትን ንብረትና ገንዘብ ይዘረፋቸዋል።  አቶ ደማሴ ገላጋይም እነዚህ የእኔ ለጆች ናቸው። ከረዥም ጊዜ ሰደት በኋላ እኔንም ዘመዶቻቸውንም ለመጠየቅ የመጡ ናቸው። እባክህ ተወን  ቢሉት እልጆቻቸው ፊት ተኩሶ ገደላቸው። ምንም እንኳን ኢሳት 'የነጻነት ታጋይ'ተሰዋ በሚል  የተሳሳተ ዜና ቢያሰራጭም ዜናው ከእውነት የራቅ ለመሆኑ በየድህር ገጹ ተነቧል። ከህይወትና ከእውነት ጋር ያልተያያዘ ፕሮፖጋንዳ ተዐማኒነትን የሚያሳጣ ይሆናል። ግንቦት ሰባትም ይህ ወነበዴ የተሰጠው ግዳጅ ቢሳካለት  የድርጅቱ ሠራዊት እንደፈጸመው ሃላፊነትን ለመውሰድና እውቅና ለማግኘት፤ በዐማራው አካባቢም ሠራዊት ያለው አስመስሎ ለመቅረብ ያደረገው የፖለቲካ ቁማር ሙከራ ሳይሳካ ከሽፏል።

ግንቦት 7 ከአንዱ ጥምረት ከሌላው ግንባር ውድቅት ሳይማር እንደገና በሻለቃ ዳዊት ወልድጊዮርጊስ አጋፋሪነት ና  በዶር ጌታቸው በጋሻው አስተባባሪነት የቅርብ ጊዜውን ፍጥምጥም አገራዊ ንቅናቄ በሚል ሰይመው የተለመደ ግርግራቸውን ጀመረዋል።

አንድ ዐይነት ላባ ያላቸው ወፎች አንድነት ይበራሉ(Birds of the same feather flock togeather)፤ የሚሉት የፈረንጆች የአነጋገር ዘይቤ  አለ። ይህ ዘይቤ በተለይም በአሁኑ ወቅት ላሉ የአገራዊ ንቅናቄ ተዋንያኖች በቂ ምሳሌ ይመስለኛል።

በዚሁ ንቅናቄ ውስጥ ያሉ እንድነ ሌንጮ ለታ (ዮሐንስ ለታ)፤ ዲማ ነገዎ (ዮሐንስ ነገዎ)፤ ብርሀኑ ነጋ፤ ዳዊት ወለደጊዮርጊስ፡ ጌታቸው በጋሻው የመሳሰሉት የቋመጡበትን የስልጣን ጥም ለማርካት ያላሴሩት ሴራ ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም ማለት ይቻላል።ሆኖም የሞከሩትን ሁሉ ሞክረው ሳይሳካ ቢቀርም ዘንድሮ ደግሞ ሌሎችን በማካተት አገራዊ ንቅናቄ የሚል ይዘው ቀረበዋል። ጥምረት ሆነ ውህደት መፍጠር ቀላል ይሆናል። ነገር ግን ተገባር የእውነት ምስክር ናትና በተገባር መተረጎሙ የከበዳል።

ይህ የተደረገው ፍጥምጥም የጫጉላ ጊዜውን ሳየጨርስ መካዳዳት እንደታዩ ሻለቃ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ ዐድራ(ዐማራ ድምጽ ራድዮ) ጋር ባደረጉት ቃለ መጠይቅ  ፍንትው ብሎ ታየቶል።እንደ እርሳቸውም አገላለጽ  የአገራዊ ንቅናቄ ባለቤቶች ግንቦት 7 እና የሌንጮ ለታ ኦዴግ እንድሆኑና የንቅናቄውንም ደንብ አርቃቂዎችና ተካፋዮችን መራጮች እነርሱ እንደሆኑ ገልጸዋል።ያረቀቁትም ድንብ የማየሻር የማይለውጥ እንድሆነና ወደንቅናቄው የሚመጡ ሁሉ ለደንቡ ተገዢ መሆን እንዳለባቸው ተገልጿል። ሻለቃ ዳዊት በሁለቱም ወገኖች ለስብሰባው ፋሲሊቴተር እንዲሆኑ በመጠይቃቸው ፈቃደኛ ሆኑ እንጂ በአባልነትም ሆነ በባለቤትነት ምንም ድርሻ እንደሌላቸው ለታሪክ አስመዝግበው የጉዳዩ ባለቤቶች ሁለቱ መሆናቸውን አበክረው አስገንዝበዋል።

በርግጥ ሻለቃ ዳዊት በወታደርነታቸው ለአርንጓዴ፤ቢጫ ና ቀይ ቀለም የኢትዮጵያ ባንዲራ ክብርና ልዕልና ህይወትን ያህል መሰዋዕትነት ለመክፈል ቃል መግባታቸውን ቢጠቅሱም የአንግ ባንዲራ  ዙሪያውን በከበበው ጠርጴዛ ተመረኩዘው መቀመጣቸው የቃል ኪዳን አክባሪነታቸውን እጥያቄ ውስጦ ሳይጥለው አልቀረም።ለኢትዮጵያ ቆሜያለሁ ለዳር ድንብሯ መሰዋዕት እሆናለሁ፣ለሰንደቀዐላማዬ እሰዋለሁ ብሎ ቃል ከገባ  አንድ የጦር መኮንን በተቃራኒው መጠበቅ  አስቸጋሪ ይመስላል። ለኢትዮጵያ ባንዲራ ጥላቻና ንቀት ያላቸው እነሌንጮ ለታና ብርሃኑ ነጋ ስዊድን ባደረጉት ስብሰባ ባንዲራውን ላለማየትም ሆነ ላለማሳየት በሸራ መሳይ ጨርቅ ጥቅልለው መታየቱ ብዙ ኢትዮጵያዊያኖች  አስከፍቷል። ከፍተኛ ብዛት ያላቸው አስትያየት ሰጭዎችም ንቅናቄው ስራውን ሳይጀመር ያሳየው የባንዲራ ጥላቻ ሁሉም ነገር ከመጀመሩ በፊት እንዳለቀ ማሳየቱን ይጠቁማሉ።

ሻለቅ ዳዊት ወልደጊዮርጊስ የአገራዊ ንቅናቄ ጉባኤ መስራች መደረክ ላይ አንድ የግንቦት 7 አባል የሆነ ግለሰብ ሃምሳ ሚሊዮን ገደማ የሚደርሰውን የአማራው ህዝብ ይወክላል በሚል ማስተዋውቃቸው በአማራው ሕዝብ ላይ እርሳቸውም እንዳሌሎቹ ጥላቻና ንቀት እንዳሳደሩ ድርጊታቸው ያሳብቃል። በ1989 ዖ.ም. በችኩልነት፤ ሁኔታዎች ፈቃጅና ወሳኝ ባልሆኑበት፤በቂ ዝግጅትን አማራጭ ዕቅዶች ባልተነደፉበት፤በከፍተኛ የኢትዮጵያ መኮንኖች የተካሄደው ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ውድቀት ሻለቃ ዳዊት ውልደጊዮርጊስን ከሻቢያ ጋር በማጣመር ተጥያቂ የሚያደርጓቸው  እትመቶች ተነበውል። በተለይም በዐማራው ሕዝብ ላይ ጥላቻና ቂም እንዳላቸው ጥቋሚ የሚሆነው፤ በ1988 ዖ.ም እንድ አውሮፓውያን አቆጣጠር በጻፉት የደም እንባ (The Red Tears)በሚለው መጽሀፍ ገጽ 17 የሚከተለው ይነበባል። "For me and others, Mengistu was the best choice for several reasons. He had come from a poor family background and was not an Amhara, the dominant ethnic group under Haile Selassie. As a person and as a junior officer he represented our rejection of past values. he would bring about a greater sense that all Ethiopian were equal , an end to class arrogance and racism. Many of us felt he would embody the spirit of the revolution and symbolize the change we wanted to bring about." ይህም ወደ አማርኛ ሲመለስ"ለኔም ሆነ ለሌሎች በብዙ ምክንያቶች የተነሣ የመንግስቱ መመርጥ በጣም ጥሩ ምርጫ ነበር። መነግስቱ የተገኘው እጅግ በጣም ደሃ ቤተሰብ ከመሆኑም በላይ የዐማራ ተወላጅ አይደለም።የዐማራ ህዝብ በአጼ ሐይለሰላሴ መንግስት ከፍትኛውን ድርሻ  ይዞ የነበረ ነው። እንደ ግለሰብነቱና እንደ ዝቅትኛ መኮንንነቱ እብሪተኛና ዘረኛውን የቀድሞውሥርዐት ላይ ያልንን ጥላቻና የቆየ ፋየዳ ይውክላል። ኢትዮጵያውያን ሁሉ እኩል ለመሆናቸው ትልቅ ስሜት በሁሉም ላይ እንዲሰፈን ሰለሚያደርግ

የእብሪተኛውና የዘረኛው መደብ ፍጻሜ ይሆናል። ብዙዎቻችን የተሰማን የአብዮቱ መነፈስ የሚያቀፈውን ስሜት መንግስቱ በመያዙ እንዲመጣ የፈለግነውን ልውጥ ይወክላል።"

እንግዲህ ሻለቃው ከረጅም ጊዜ ጀምሮ በዐማራው ላይ ያላቸውን የተንሸዋረረ አመለካከት ማስረጃ ቢስና በታሪክም የማይደገፍ ነው።ለዚህም ዋናው ምክንያት በዐጼው ዘመነ መንግሥትብርግጥ ከተገፉትና መከራና ስቃይ ከሚደርስባቸው ሁሉ በዐማራው ላይ ይደርስ የነበረውን ሰቆቃና ዋይታ መካድ አይቻልም።ያልነበረውን እንደነበረ አንሸዋሮ ማየት ሊመነጭ የሚችለው ከጥላቻ ወይንም ጥላቻ ባላቸው ዘንድ ርካሽ ተወዳጅነትን ለማትረፍ ከሚሹ ብቻ ነው። ዐማራው ከሌሎች እትዮጵያውያን ሁሉ በነበረው ስርዐት ተጠቃሚ ነበር የሚለው አስትያየት የዐማራውን ህልውና የሚፈታተን ከመሆኑም በላይ የዐማራውን ታሪክን ጥላሸት ለመቀባት የሚደረገው ሙከራ ሁሉ የጠባብ ብሄረተኞች ጊዜው ያለፈበት ስልት ከመሆን ባሻገር ከታሪክ ያልተገናዘበ ከዕውነትም የራቀ ነው።

በማጠቃለያም የግንቦት 7 እና የነሌንጮ አገራዊ ንቅናቄ በሚል የእናሞኛችሁ ግርግር ሲታይ፤

- ብርሃኑም ሆነ ሌንጮ በዲያስፖራው ዘንድ ተቃዋሚ መስለው ይቅረቡ እንጂ ከሚያደርጉት የተገባር እንቅስቃሴ፤ ከሚፈጥሯቸው ስምምነዮች አኳያ ሲታይ ባለው መንግስት ላይ ተጸዕኖ በመፈጠር ወደ ሃገር ቤት ለመገባት እየፈጠሩት ያለ መንገድ ይመስላል፤ነጻነትን እንገናጽፍሃልን ገነዘብ አምጣ እያሉ የሚቦጠቡጡትን ህዝብ መናጆ አድርጎ ከመደለል በስተቀር ምንም አይፈይዱለትም"።
- ሌንጮ ለታ ላለው መንግስት ባለውለታ ለመሆኑ በእራሱ አንደበት በኢሣት ቴሌቭዥን ቀረቦ የኢትዮጵያ መንግሥት አሁን የሚገዛበትን ሕገ መንግሥት አዘጋጅቶ በማቅርብ የጌቶቹን የመለስ ዜናዊንና የኢሣያስ አፈውርቂን ይሁንታ ተሰነዩ ከተባለው *ሥፍራ* እንዳገኘ፤
- ብርሃኑ ነጋና ሌንጮ ለታ ለማስመሰል ተቃዋሚ ሆነው ይታዩ እንጂ ምስጥራዊ የሆነ ግንኙንት ከገዢው መንግሥት ጋር ይኖራቸው የሆናል የሚል ጥርጣሪ ያጭራል።
- ሌንጮ ባለውለታቸው ህግ መንግሥት አርቃቂያቸው ከመሆኑም በላይ ባለው መረጃ አሁንም ከወያኔ ጋር በየጊዜው በተለያየ መነገድ እንደሚገናኝ ታውቋል።
- በሌላም በኩል የግነቦት 7 እን በየጊዘው የሚፈጥራቸው ጥምረቶችና ህብረቶች ምን ያህል ግባቸውን ሳይመቱ መቅረታቸው የተደረጉት ስምምነቶች ያለተሟላ አንድ ችግር እንዳለባቸው መገመት ይቻላል። ይህም እየጠቅመ ያለው የውያኔን መነግስት ብቻ ነው። ለዚህም ኢሣት የአንበሣውን ድርሻ አስተዋጽኦ አድርጓል። ባብዛኛው ዕጅ ያደረጋቸው እንቅስቃሴዎች የእነ ብርሃኑን ትክለ ሰውነት ከመገንባ የራቀ ባይሆንም ከዕውነት የራቀ ባይሆንም የተግል አቅጣጫን ጠቋሚ ያልሆነ የፐሮፖጋንዳ ዘመቻ ማድረጉ ዲያስፖራው ትክክለኝ ገጽታውን እንዳይመለከት አድርጎታል።
- መንግስትም በሜዳው የሚደረግውን እንቅስቃሴ እንደመንግስትነቱ በቂ መረጃ የለውም ማለት አይቻልም። ይህም የግንቦት 7ን ጥንካሬ ድከመት የዲያስፖራውን ጥንካሬና ደከመት ወዘተ. በሌላም በኩል በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ ተከፋፍሎ ድልን መቀዳጀት አይቻልም።ስለዚህ ተባበሩ ወይንም ተሰባበሩ የሚለው ቋንቋ ወያኔን ያስበረግገዋል። በመሆኑም ዲያስፖራውን ለመከፋፈል ዲያስፖራውን መስለው የሚንቀሳቀሱ ስረጎገቦችን ማሰማራት አንዱ ተገባሩ ነው።

ሁለተኛው ደገሞ በዲያስፖራው ውስጥ ከሚንቀሳቀሱ ድርጀቶች መካከል አንዱን አግዝፎ በማሳየት የፕሮፖጋንዳ ስራው ትኩረትም በዚሁ አቅጣጫ እንዲሆን ማደረግ ነው ። ይህ የሚጠቅመው በድርጀቶች መካከል አላስፈላጊ ሽኩቻን ጥላቻ እያየለ እንዲመጣ ነው። ለዚህ ጉልህ ማሰረጃ የሚሆነው የግንቦት 7 ድርጅት ነው። ይህ ድርጀት ይህ ነው የሚባል የጎላ የፖለቲካም ሆነ የወታደራዊ ስራ በታሪክነት ሊጠቅስ የሚችል ያከናውነው የለም። ነገርግን ወያኔ ይህን ድርጀት አተኩሮ የፕሮፖጋንዳ ስራ የሚሰራበት እውነት ድርጀቱ ጉዳት አድረሶበት ሳይሆን እላይ በተጠቀሰው መሰረት ዲያስፖራው አንድነቱን እንዳያጠናክርና ራስ ምታት እንዳይሆንባቸውነው።

- ኢሳት ምንም እንኳን ሙሉ ነጻነት ባይኖረውም ከድርጀት ጥገኝነት ወጥቶ በነጻነት ቢሰራ ተጽእኖ አድራጊነቱን መገነዘብ ይቻላል።ለሃገር ናፋቂውም ህዝብ የምንመኘውን ለውጥ በማምጣት አኳያ አስተዋጾ ይኖረዋል። በመሆኑም አገር ወዳድ የሆነ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የዚህ ሃሳብ እንዲሳካ የየብኩሉን ድርሻ መወጣት አለበት።

- ወያኔ ኢሃድግ ግንቦት 7 በኢትዮጵያዊነት ላይ ባለው አመለካከት፤ ከሻቢያ ጋር ባለው ሥምምነት፤ከዲያስፖራው ጋር ልዩነት እንዳለው በውጭ ከሚኖርት ኢምባሲዎችም ሆን ካስማሯቸው ስላዮቻቸው ይገነዘባሉ። በፕሮፖጋንዳቸው አጉለተው የሚያሳዩት ሆን ብለው የተቃዋሚው አንድነት እንዳይመጣና መከፋፈሉ እንዲጎላ ነው። በሌላም በኩል በሻቢያና በወያኔ መካከል የማይታረቅ ቅራኔ ያለ እያስመሰሉ የሚያወሩ አሉ። ሌባ ሲሰርቅ ተስማሞቶ ሲካፈል የጣላል እንዲሉ በነዚህም መካከል ያለው ይህ ሆኖ በመሪዎቹ መካከል ያለ መናናቅ እንጂ ዐላማቸውን አደጋ ላይ የሚጥል ቅራኔ የለም።

ሰው የትላንት ወዲያውየተግባር እንቅስቃሴ ለትላንቱ ፤ የትላንቱን ደግሞ ለዛሬው፤እንዲሁም የዛሬው ለነገው ታሪክ አድርጎ ማየት የሚችል ከታሪክ የሚማር ማስተዋል ያለው ፍጡር ነው። ከታሪክና ከህዝብ ተሰውሮ መኖር አይቻልም። መቸገ የለመደ እናቱን ያሰማማል እንዲሉ የሥልጣን ጥም ለማርካት ከለየለት ጠላታችን ከኢሣያስ አፈወርቂ እና ከታሪካዊ ጠላቶቻችን ጋር መሞዳመድ ከንቱነት ነው።

ጎቾዬ እንግዱ

ከሊቭላንድ ኦሃዮ